# በፈርዖን መንፈስ

የተወደዳችሁ ወገኖቼ! "ኢትዮጵያዊ ቁልፎች" የሚለውን ጽሁፍ ከፃፍኩ በኋላ እጅግ በርካታ መልክቶች ደርሰውኛል። ለቻልኩት ያህል መልስ ለመስጠትም ሞክሬአለሁ፤አንዳንዶች ደግሞ ለምን በእንግሊዝኛ አትፅፍም ብላችሁ ለጠየቃችሁኝ የእኔ ዋናው ፍላጎት መልእክቴን ለሃገሬ ልጆች ማድረስ ሲሆን ከዚያ በመቀጠል ደግሞ በኢትዮጵያዊ ማንነቴ የምኮራ ስለሆንኩና ማንነቴንም ስለማከብር ነው፤ ለምሳሌ ብዙ ጊዜ አስተውላችሁ ከሆን አንዳንድ የሃገር መሪዎች እንግሊዝኛውን እያወቁት ነገር ግን የሚጠቀሙት በሃገራቸው ቋንቋ ነው፤ ይህም የራሳቸውን ማንነት ከማክበር የመነጨ ነው። ስለዚህም ችሎታው ቢኖረኝና በሌላ የሃገሬ ቋንቋ ብጠቀም ደስ ባለኝ፤ ነገር ግን በሌላ የባዕዳን ልሳን ልጠቀም አልችልም።

ብዙዎች ወንድሞቼና እህቶቼም ለፍቅር፣ ለእርቅና ለመግባባት ያሳያችሁትን አቋም አደንቃለሁ፤ ከምንም በላይ በአገዛዝ ላይ ያለው የክፋት ቡድን ውስጥ ሆናችሁ አስደናቂ መልእክቶች ለላካችሁልኝ ግለሰቦች የነፃነት ደወል በበራችሁ እንዳንኳኳ ግልፅ ነው፤ ማድረግ ያለባችሁም ከወገናችሁ ጋር በፍቅር መሰለፍና ወገንን በመጨቆን ከሚገኝ ተድላ ደስታ መራቅ ነው። ያለባችሁንም የውጥረት፣ የቀንበር መጠን ስላካፈላችሁኝም አመሰግናለሁ። የዚህን ጽሁፍ ርዕስ "በፈርዖን መንፈስ" ያልኩበት ምክንያትም በአገራችን ያለው የወገኖቼ ቀንበር ስለበዛ ይህንን ለመግለጽ ነው። ይህንን ጽሁፍ ከበፊቶቹ ለየት የሚያደርገው በመንፈሣዊ ተመስጦ የተፃፈ መሆኑ እና ጠንካራ የተግሳፅ ቃላትን ያዘለ መሆኑ ነው። እንደተለመደውም ይህንን ጽሁፍ አንብባችሁ ይጠቅማል፣ ያንፃል ያላችሁትን እንድትወስዱ ለሌላውም እንድታቀብሉ ብዬ እንድታነቡልኝ በድጋሚ በፍቅር እጠይቃለሁ።

የሕዝባችን መከራ በዝቷል፤ ሁሉም አንገሸግሾታል፤ ጥልቅ ሃዘን ላይ ነን፤ ለምን አንሆን? ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ሆነን እናት ሃገራችንን ባሰብናት ጊዜ ሁላችንም እንባችን በጉንጫችን እንደወረደ ይኸው አለን። በሃገሬ ያለው፣ በክፋት መንፈስ የሚመራው የአገዛዝ ቡድን እለት እለት በወገኔ ላይ የሚያደርሰው ጭቆና እጅግ እያቃጠለኝ ነው፤ እኔ ሰላማዊ ሰው ነኝ፤ ምክሬም ፍቅር ነው፤ ይህንን የንዴት ስሜቴን ግን ለመደበቅ ተቸግሬአለሁ። ቂም እንዳልይዝ፣ ቂም አላውቅም፤ ቤተሰቦቼ ሲያሳድጉኝ ሁሉን አክብሬ፣ ሁሉን

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

ወድጄ፣ለሁሉ እጅ ነስቼ ንወር ክበር ብዬ እንድኖር እንጂ እንዳቄም አይደለም። እንዳልበቀል ለበቀል የሚጠነክር ልብ የለኝም፤ እንደውም እውነቱን ለመናገር በቀል እንዴት እንደሆነ አላውቅም፤ የማደርገው ጠፍቶኛል፤ ግን ውስጤ ስለ ውዷ እናት ሃገሬና ወገኖቼ እየተቃጠለ ነው።

ሁሌም እንደማደርገው መሸሸጊያዬ፣ አለቴ አምላኬ ነውና ለመፅናናት ያህል ቅዱሱን መፅሀፍ ከፈትኩኝ፣ እንዲህም አነበብኩኝ፤ *"የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ፣ ሕዝቡንም አልለቀቀም"* ዘጸአት 9፣7። ይኽንን አጥቅሼ ስለ ሃገሬ ሁኔታ በመንፈስ እመሰጥ ያዝኩኝ፤ ጥያቄዎች በውስጤ ይመላለሳሉ፤ በርግጥ የአገራችን አገዛዝ በፈርዖን መንፈስ እየተነዳ ይሆን? ደግሞስ ፈርዖን የሌላ ምድር ሕዝብን ነው እኮ አልለቅም ያለው፤ እና እኛ በራሳችን ወንድም በእናታችን የአብራክ ክፋይ እኮ ነው የተያዝነው። ኧረ! ይሄ ለሰሚ እንኳን ከባድ ነው! ሰው እንዴት ወንድም እህቶቹን የእናቱን ልጆች ያሰቃያል? በየትኛውስ አንጀቱ ቻለው? ወይስ ከእርሱ ጀርባ ሃገሪቱን የሚመሩ ባዕዳን ይኖሩ ይሆን? ለዚህ ይሆን ስለ ስልጣን መልቀቅ ሲነሳ እርግጠኛ ሆኖ መናገር የማይችለው? አዋቂው እግዚአብሔር ብቻ ነው። አጠቃላይ የሃገራችን ሁኔታ ያስፈራል፤ የመብራቱና የውሃው ቅጣት እንዳቅለሸለሻቸው ብዙዎች ነግረውኛል፤ የኑሮው ነገር ሊወራ ከማይቻልበት ደረጃ ደርሷል፤ሕዝቡ ግራ ተጋብቷል፣ ፋብሪካዎች ቆመዋል፣ ንግዱ ቀዝቅዟል፣ ሰዉ እጅግ ተከፍቷል፣ ራሱ የመንግስት ሰዎችም እራሳቸው እየተንገፈገፉ ነው፣ ሃገሪቷ በየቀኑ የሕግ ጋጋታ ስለሚወጣባት የታፈነ ቤት ሆናለች።

ወደ እናት ምድራቸው ለመመለስ ከተነሳሱት አንዱ እኔ ነኝ፤ የሃገሬ ትዝታ ሁሉ በአይኔ ላይ በዝቷል፤ አሁንማ ይኼንን ነገር መቆጣጠር ስላቃተኝ በየድህረ-ገጹ ሁሉ፣ *"ዘጸአት"* እያልኩ መለፍለፍ ጀምሬአለሁ። ለነገሩ ያንን የመሰለ ገነት ሀገር እያለኝ እዚህ በሰው ሀገር እላይ ታች የምለው! ለምቾቱማ ቢሆን ኖሮ ከማንም ኢትዮጵያዊ በላይ የተንደላቀቀ ሕይወት ነው ያለኝ፤ ቁም ነገሩ እርሱ አይደለም እንጂ። ወደ ዋናው ሃሣቤ ተመለስኩኝ፣ እፀልይ ገባሁ፤ *"ጌታ ሆይ እስከ መቼ ግን ትረሳናለህ? እስክ መቼስ የሕዝብህ መከራ ችላ ይባላል? አንተ ሳታውቅ ምን የሚደረግ ነገር አለ? አምላኬ ምን አስበህ ይሆን፣ ይሄ ሁሉ ቀንበር በራሳችን ሲጫን ምነው ዝም አልክ?"* እንዲህ እያልኩ መመሰጤን ቀጠልኩ።

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

**ወይ ጉድ!** የበለጠ ሕዝቡ ኃይል የሌለው እየሆነ ሲሄድ፣ የክፋት ቡድኑም ጨቋኝ እየሆነ ሄዷል። እግዚአብሔር ያገለግለኝ ዘንድ፣ ደስ ብሎት ወደ ማደሪያዬ ይመጣ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ ካለ ቆይቷል፤ ነገር ግን ይኼ አገዛዝ በአንድ አቋም ፀንቷል፤ እንዲህም ማለት አብዝቷል፤ " ቃሉን እሰማ ዘንድ እግዚአብሔር ማነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፣ ኢትዮጵያንም አልለቅም። እንደውም ክንዴን የበረታ አደርገዋለሁ፤ በሕጎቼ አሸብረዋለሁ፣ በአሽከሮቼ አጎሳቁለዋለሁ፣ በረሃብ እገርፈዋለሁ፣ በጨለማ አስውጠዋለሁ፣ ደስታውን እነፍገዋለሁ፣ ማንም ቀና ብሎ ሊናገረኝ ቢያየኝ ወደ እስር ግዞት እወረውረዋለሁ፣ ልጓማችሁንም አጠብቃለሁ፣ የጥፋት ልጅ ነኝና ምድሪቷን አውድማታለሁ፣ የምድር ሲኦል አደርጋታለሁ፤ ስለዚህ አምላኬ! አምላኬ! የምትለው መጥቶ ያድንህ፤ እኔ በፈርዖን መንፈስ እገዛችሂለሁ።" እያለ ነው።

በጥበብ ሆኖ ይህን ነገር ለመመርመር ብዙ ጊዜ አይፈጅም፤ እግዚአብሔር በፀናች ክንዱ ከባርነት፣ ከዘረኝነት፣ ከተገዥነት በተዘረጋ ክንድ፣ በታላቅም ፍርድ ሊታደግህ ሲዘጋጅ የጠላትህን ልብ የደነደነ እና በአንተ የጨከነ ያደርገዋል። በዚህም ጊዜ ረዳት የለህምና አጋዥ መተማመኛህ፣ መሸሸጊያህ ፈጣሪህ ነውና፣ አቤቱ! ወደ እኛ ተመልከት፣ ስድብ እንደሸክም ከብዶናልና፣ ከመከራችን የሚታደገን የለምና፣ አሁንስ ተስፋችን ማነው? አንተ አይደለህምን? ትዕግስታችንም ከአንተ ዘንድ ነው ትላለህ፤ በዚህ ጊዜ ያለህን መተማመኛ አሟጠህ ወደ ፈጣሪህ ብቻ ስታንጋጥጥ እርሱም ፊቱን ወደ አንተ መልሶ "ሕዝቤ ሆይ ስለምን ትሸበራለህ? ስለምንስ ታለቅሳለህ? አንተ በፍቅር በአንድነት ሆንህ፣ በአንድ ልብ በአንድም ድምፅ ወደ ፈርዖንህ ሂድ፤ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፤የምትናገረውን አስተምርሃለሁ፤ አንተም ልቀቀኝ ትለዋለህ፤ እኔ ግን በፈርዖን ፊት የማደርጋትን ተአምራት አይተህ ስሜን ለዘለዓለሙ ትቀድሳት ዘንድ የእርሱን ልብ አጸናዋለሁ፣ ሕዝቡንም አይለቅም።" እኔም ለፈርዖንህ እንዲህ እንዋለሁ፤"ኢትዮጵያ የተመረጠ ልጄ ነው፣ ሳያየኝ የሚያምነኝ ነው፣ ተቸግሮ የሚያመሰግነኝ ነው፣ጦርነት ሲመጣ የቃል ኪዳኔን ታቦት አዝሎ የሚወጣ ነው፣ ኢትዮጵያ ለማንም የማይገዛ በእኔ ንግሥናና ልእልና የሚኖር ነፃ ሕዝብ ነው፣ከአባቱ ኢትዮጲስ ከተባለው መልከ ጼዴቅ ጀምሮ የእኔ ሕዝብ ነው፣ እጆቹን አንድም ለምስጋና አንድም ለልመና ወደ እኔ ወደ አምላኩ የሚዘረጋ ልጄ ነው፣እለት እለት ስሜን በማደሪያዬ የሚጠራ፣ አኗኗሩ ከእኔ ስርዓት ያልተዛነፈ ልጄ ነው። ለምን ይመስልሃል እንደዚህ ያንተን፣ እንዲሁም ካንተ በፊት የነበረውንም ፈርዖን ልብ አደንድኜ ጨካኝ አድርጌ የነበረው? ለምን ይመስልሃል እናንተን ለቅጣት አዘጋጅቼ የነበረው? ሕዝቤ ላለፉት አራት አስርት አመታት እኔን አምላኩን ረስቶ ለማይረቡ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

ለምናምንቴ ጣዖቶች (እግዚአብሔር የለም በሚሉ ሃሳቦች) ተገዝቶ ስለኖረ ነው። በውኑ ቆንጆ ጌጥዋን ወይስ ሙሽራ ዝርግፍ ጌጥዋን ትረሳለችን? ሕዝቤ ግን የማይቆጠር ወራት ረስቶኝ ነበረ፡ አሁን ግን ኤሎሄ! ኤሎሄ! እያለ ወደ እኔ ጮ኿ል፤ የጩኸቱም ድምፅ ከእኔ ዘንድ ከአርያም ደርሷል። የወጣቶቹን የእስር ግዞት ተመልክቼአለሁ፣ የእናቶችን እንባ አይቼአለሁ፣ የአዋቂዎቹን የምሁራኑን ስደት፣ ከኢትዮጵያ ማዶ ያሉትን የሴቶች ልጆቼን መከራ አስቤአለሁ፣ የምድሪቱን ዋይታ የሕዝቡንም ልቅሶ ሰምቼአለሁ፤ ስለዚህም ይገዛልኝ፣ ያከበረኝ ዘንድ የተመረጠ ልጄን ኢትዮጵያን ልቀቅ አልሁህ አንተም ትለቀው ዘንድ እንቢ አልህ፤ እነሆ እኔ ካንተ የተመረጠውን ሁሉ እገድላለሁ፤ በውስጥህ ሰላምህን አናጋለሁ፤ በተኛህበት በህልም ውስጥ ህልም እያሳየሁ አሸብርሃለሁ፤ ስለዚህም ነገር እንደ አበደ ውሻ ሁሉን ትነክሳለህ፤ የምታምነውን ታጣለህ፤ ሕዝቤን አለቅም ብለህ የህግና የትዕዛዝ ጋጋታ ታበዛለህ። እኔ ግን በየደረስክበት ውርደትህን አበዛዋለሁ፤ ከሌሎች ነገሥታት መሪዎች ጋር ስትገናኝ ሞገስህን እገፋለሁ፤ ስለዚህም እንደ ልክስክስ ውሻ ይመለከቱሃል፤ በአስተዳደርህ ያሉትን ከአንተ ላይ ልባቸውን አዞራለሁ፤ የጦር አበጋዞችህን በትዕቢት እሞላለሁ፤በስካር እና በዝሙት መንፍስ ሞልቼ አላማቸውን አስትና ገንዘብ ብቻ እንዲያስቡ አደርጋቸዋለሁ፤ ልጆቻችሁንም አላማ ቢስ ወራዳ አደርጋቸዋለሁ፤አንዳንዶቹንም በሽተኛ አድርጋለሁ፤ አንተንም በሚጥል በሽታ አሰቃይሃለሁ፤ ርኩሱንም መንፈስ በቀኝህ አቆመዋለሁ፤ ሚሽትህንም ከበፊቱ የበለጠ አመንዝራ አደርግና አቃጥልሃለሁ።

አንተ ይኼን ሁሉ ጦር ስትሸከም፣ ይኼን ሁሉ ሃያል ክንድ፣ ይኼን ሁሉ ሰላይ ስታበዛ፤ ባላሰብከው መንገድ እንደ ዳዊት በትንሽ ብላቴና አዋርድሃለሁ፤ ጌዲዮን እንዳደረገ በጥቂት ኀበዛዝት አንድም ጦር ሳይሰበቅ ከወንበርህ እገለብጥሃለሁ። ጥላህን ከላይህ ገፍፌአለሁ እኔም ከዚህ ብላቴና ጋር እሆናለሁ፤ እርሱም ስሜን ጦር አድርጎ ተነስቷልና ኃይልና መሰማትን እሰጠዋለሁ፤ ሕዝቤንም ከመከራ ያወጣ ዘንድ አብሬው እሰለፋለሁ። በሰው ዘንድ ሞገስን እንደ እያሱ ስለምሰጠው ዝናው በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ይወጣል፤ በእጁም አንድ ጦር ወርውሮ አያውቅም እኔም ከአባቶቻችሁ ጋር እንደተማማልኩት ያደረኩትን ቃል ኪዳን ይመልስ ዘንድ ልቡን ወደ እኔ አዘንብሏልና፤ እኔ ከእርሱ ጋር እወጣለሁ ስለዚህም አንዳች አይፈራህም። አባቶቻችሁ ካደረጉት ኃጢአት አንዳች አልተባበረምና ምድሪቱን በዚህ ትውልድ አሳርፋታለሁ፤ የወገኖቹን ችግር ሲያይ ልቡ በሃዘን ተነክቷልና፣ ከሕዝቡ ጋር መከራን ሊቀበል ወዷልና፣ ስለ ስሜም ቀንቷልና በዚህ ብላቴና ትውልድ የቀድሞውን የአባቶቻችሁን ክብር እመልሳለሁ። ሳሙኤል በድብቅ አገልጋዩ ዳዊትን እንደቀባ እንዲሁ ከተመረጡት ካህናት ውስጥ በራሱ ላይ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

ዘይት እንዲያፈስበት አድርጌአለሁ፤ እንግዲህ በመንግስትህ ውስጥ መንግስት ተፈጥሯል። እግዚአብሔር ክፍሌ ነው ብሎ ተነስቷልና እኔም ከርሱ ጋር እሆናለሁ፤ በዚህ ብላቴና የተመረጠው ሕዝቤ ተፈርቶና ተከብሮ ይኖራል። እኔም እንደ ቀድሞ በረድኤት በመካከሉ እገኛለሁ፤ ሕዝቤንም ፊቱን ወደ ትጋት እመልሳለሁ፤ ከምድሩም ተቀብሮ ያለውን ሃብት በጥበቤ ያወጡታል። የሕዝቤንም ቅሪት ከአሕዛብ ዘንድ አከማቻለሁ፤ ከተበተኑበትም አገሮች እሰበስባቸዋለሁ፤ በትእዛዜም ይሄዱ ፣ ይፋቀሩና ይዋደዱ ዘንድ አንድ ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ በውስጣቸውም አዲስ መንፋስ አደርጋለሁ። ይህም ብላቴና በሰጠሁት ጥበብ ምድሪቱን አንድ ያደርጋታል፤ ካንተ በፊት የነበረው ፋርያን ሳይቀር የሸጠውን ምድር ሁላ ይመልሳል፤ የዚህም ብላቴና ትውልድ አባቶቹ አፋቸውን በእጃቸው እስኪጭኑ ድረስ ድንቅን ያደርጋል።

አንተ ግን ባትመለስ፣ በዚህም ትዕቢትህ ብትፀና አዋርድሃለሁ ከትቢያም እደባልቅሃለሁ፤ ከእኔ ቁጣ ያድንህ ዘንድ የሚችል ማነው? ሞሎክ ነው? ወይስ ሉሲፌግ? ባአል ነው? ወይስ ቤልዜቡብ ነው? ወይስ አስቴሮት ነች? ወይስ አድራሜሌክ ነው? ጠንቋዮችህን ጠይቅ፣ ከእኔ ዘንድ የሚታደግህ ማነው? እነሆ ሁሉን ያዘጋጀሁ እኔ አይደለሁም? ለመሆኑ አንተ ማነህ ስሜን የተገዳደርክ? በአደባባይ፣ በምክር ቤትህ እኔን አላውቅም ያልክ? አንተንና ግብረ አበሮችህን ለቅጣት ያዘጋጀሂችሁ እኔ አልነበርኩም? አንተንስ ከዛ እንደ አራዊት ከተመሰግክበት ጉድጓድ አውጥቼ እዚህ ያስቀመጥኩህ የሕዝቤ ኃጢአት አሳዝኖኝ አይደለም?።

አሁን ግን ልጅ ወደ አባቱ ቤት እንዲመለስ ሕዝቤም ልቡ ወደ እኔ መጥቷል፤ መታመኛው እኔና እኔ ብቻ እንደሆንኩ አውቋል፤ ወርቅ በእሳት እንዲፈተን እኔም ልጄን ኢትዮጵያን ልዩ ልዩ በሆነ መከራ ፈትኜዋለሁ፤ የታመነ ወዳጅ ሆኖም አግኝቼዋለሁ፤ በሌሎች የአሕዛብ ነገሥታት መመካቱን ትቶ ወደ እኔ ተመልሷል፤ ስለዚህም ነገር በቃሌ ብቻ ኑ! እንውረድ! የተመረጠው ሕዝባችንን እንታደግ ብዬአለሁ። እንግዲህ ወዮላቸው! አብረውኽ ለሚያጨበጭቡ፤ እንግዲኽ ወዮላቸው! የወገናቸውን ችግር ከምንም ሳልቆጠሩት፤ እንግዲህ ወዮላቸው! አባቶችህ የሰጡህን ድንበር ስታፋልስ ይሁን ብለው ለመረቁህ፤ እንግዲህ ወዮላቸው! ወጣቶቹ ሸሽተው ወደ ማደሪያዬ ሲገቡ ሳስፈጇቸው፤ እንግዲህ ወዮላቸው! ሕዝቤ ተርቦ መሬቱ ለሌላ ሲሰጥ አዎ! ትክክል እያሉ ለጮኹ፤ ቁጣዬ ከላይ እንደሚያገሳ አንበሳ ሆኗልና፤ ካንተ ጋር ያሉት ሁሉ እኔን ለማወቅ ባልወደዱ መጠን የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

*አእምሮአቸውን ለማይረባ ነገር አሳልፌ የሰጠሁባቸው ናቸው፤ ስለዚህም የጥፋታቸው ቀን እጅግ ቅርብ ነው።*

*ነገር ግን አንተ በፈርዖን መንፈስ ያለህ ሰው! እኔ እኮ እንተን ያስነሣሁህ ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ ስሜም በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ፤ ከአባቶቻቸው አባት ከመጀመሪያው አንሥቶ የብሔሩ ገዢ ንጉሣቸው፣ ታዳጊያቸው እኔ መሆኔን ያውቁ ዘንድ እኮ ነው። ነገር ግን ከሚቻላቸው መጠን ይልቅ ይፈተኑ ዘንድ የማልፈቅድ፣ እኔ አምላካቸው እግዚአብሔር የታመንኩ ነኝ። ይታገሱም ዘንድ እንዲችሉ ከዚህ ሁሉ ፈተና ጋር መውጫውንም ደግሞ አድርጌላቸዋለሁ፤* ***በዚህም ብላቴና የማደሪያዬ ካህናት እንኳ የሌላቸውን ጥበብ አድርጌ ሕዝቡን ነፃ አወጣዋለሁ፤*** *እነርሱም በስሜ ተጠርተዋልና አልተዋቸውም።"*

ከመንፈሳዊ ተመስጦዬ ነቃሁ፤ አሰላሰልኩ፤ በሕይወቴ ውስጥ ብዙ መልስ ያላገኘሁላቸው ነገሮች አሉ፤ ነገር ግን እንደ እናት ኢትዮጵያ መልስ ያጣሁበት ነገር አልነበረም። አሁን ግን መልሱን አግኝቼአለሁ፤ መልስ ሁልጊዜም ከፈጣሪ ነው፤ የተደበቀውን የሚገልጥ እርሱ ብቻ ነው። ***እግዚአብሔር ስራውን በማይገመት ሰው እንደሚሰራ አምናለሁም አውቃለሁም።*** በሃሣብ ሀገሬ ገባሁ፤ ፍቅር እና አንድነት፣ ይቅር መባባል፣ ክፋትን ማስወገድ..... ብዙ ሃሳቦች፤ አልጋዬ ላይ ሆኜ አይኔን ከመጨፈኔ በፊት መጽሐፉን ገለጥኩት እንዲህም አነበብኩ፤

*"እግዚአብሔርም ሙሴን እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ፣ ውኃውም በግብፃውያን በሰረገሎቻቸውም በፈረሰኞቻቸውም ላይ ይመለስ አለው። ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፣ ባሕሩም ማለዳ ወደ መፍሰሱ ተመለሰ፤ ግብፃውያንን በባሕሩ መካከል ጣላቸው። ውኃውም ተመልሶ በኋላቸው ወደ ባሕር የገቡትን ሰረገሎችን፣ ፈረሰኞችንም የፈርዖንንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ፤ ከእነርሱም አንድ ስንኳ አልቀረም። የእስራኤል ልጆች ግን በባሕሩ ውስጥ በየብስ ሄዱ፤ ውኆችም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆኑላቸው። እግዚአብሔር በዚያ ቀን እስራኤልን እንደዚህ ከግብፃዊያን እጅ አዳነ፤ እስራኤልም የግብፃውያንን ሬሳ በባሕር ዳር አዩ። እስራኤልም እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያደረጋትን ታላቂቱን እጅ አዩ፣ ሕዝቡም ፈጣሪያቸውን ፈሩ፤ በእግዚአብሔርም በባሪያውም በሙሴ አመኑ።"*

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)

እኔም ያችን ቀን የሃገሬ ፈርዖን የሚሰጥምባትን የታላቅ ተአምር እለት እያለምኩኝ ስለ እነ ቴዲ አፍሮ፣ ስለ እነ ቡርትካን፣ በእስር ስላሉት አዛውንቶች፣ አነግ፣ቅንጅት፣ግንቦት 7፣ምናምን እየተባሉ ስለታሠሩ ብዙ ወጣቶች፣ ስለ ቤተ- እግዚአብሔር ትርምስ፣ ስለ ሕዝቡ ቀንበር በእጅጉ አሰብኩኝ...

ቴዲ አፍሮ ግን ማንም ሳያስተውል ትንቢት ተናገረ፤ እንዲህም እያለ
*ጃህ ያስተሰርያል! ጃህ ያስተሰርያል!.........*
***ዘጸአት ለኢትዮጵያ ወደ ተስፋ ጉዞ***
***ባሕሩን 'ሚያሸግር አንድ ሙሴ ይዞ***
***ቅርብ ነው አይርቅም፤ የኢትዮጵያ ትንሳዔ***
***ባንድነት ከገባን፤ የፍቅር ሱባዔ***

*ሀገሬን ማሰብ ቀጠልኩኝ፤ አልገለጥ ብሎን እንጂ ሀገራችንስ የምድር ገነት ናት።*
በርቱ አይዟችሁ! ልባችሁም ይጽና የሀገሬ ልጆች! ስለ ሁሉ ፀልዩ።

ቸሩ ፈጣሪያችን ሀገራችንና ሕዝባችንን ሁሉ ይባርክልን፤

***እኛ ታላቅ ነን! ልባችንም!***
በትረ ሙሴ

Create PDF files without this message by purchasing novaPDF printer (http://www.novapdf.com)